በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

ደብረ-ዘይት

ደብረ-ዘይት ማለት የወይራ ዛፍ ተራራ ማለት ሲሆን /ደብር-ተራራ ፡ ዘይት-የወይራ ዛፍ/ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ከጎልጎታ ቀራንዮ በስተምስራቅ የሚገኝ ታላቅ ተራራ ነው፡፡ ይህ የደብረ-ዘይት ተራራ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ የሚያስተምርበት፣ ውሎ የሚያርፍበት እና እየጸለየ የሚድርበት ስፍራ ነው፡፡ ጌታችን ያረገውም በዳግም ምጽአት ለፍርድ የሚመጣውም በዚሁ ተራራ ላይ ነው፡፡ /ሐዋ 1 ÷ 13/ እንግዲህ በቤተ-ክርስቲያን ስርዓትና አስተምህሮ መሰረት የአብይ ጾም 5ተኛው ሳምንት ‘ደብረ-ዘይት’ ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ጌታችን በደብረ-ዘይት ተራራ ላይ ሆኖ ለቅዱሳን ሐዋርያቱ ስለ ዓለም ፍጻሜ፣ በግርማ መለኮት ስለሚሆን ስለ ዳግም ምጽአቱ እና አስቀድመው ስለሚታዩት ምልክቶች አስተምሯል፤ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያናችንም የዐቢይ ጾም እኩሌታ በሆነው በዚህ ሳምንት ይህን የጌታን መምጣት ከዘመን ዘመን ለልጆቿ ስታስተምር ትኖራለች፡፡ ስለ ጌታ መምጣት የሚሰብከው የደብረ-ዘይት ምስባክም ይህ ነው፡- መዝ 49÷ 3

እግዚአብሔርሰ ገሃደ ይመጽዕ፤ እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል፤

ወአምላክነሂ ኢያረምም፤ አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም፤

እሳት ይነድድ ቅድሜሁ፡፡ እሳት በፊቱ ይነድዳል፡፡

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 24 ÷ 3 ላይ ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታን "የመምጣትህና የዓለም ፍጻሜ ምልክቱ ምንድነው ?" ብለው ሲጠይቁት የማይቀረውን የዓለም ፍጻሜ ምልክቶች አስቀድሞ ነቢያቱን ልኮ ካስተማረውና በዘመኑ እየሆነ ካለው በማመሳከር በዓለም ፍጻሜ ምን እንደሚከሰት አስተምሯቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

- ብዙዎች 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ በስሜ የመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡
- ህዝብ በህዝብ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳል፤ የጦርነትንም ወሬ ትሰማላችሁ፡፡
- ርኩሱም በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ ታያላችሁ፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም አሁን በዘመናችን የምናያቸውን ምልክቶች ጌታ አስተምሯቸዋል፡፡

የአለም ፍጻሜ ሲቀርብ ከሚታዩ ነገሮች መካከል አንዱ የሐሳዊው መሲህ መገለጥ ነው፡፡ ይኸውም ሐሰተኛ የሆነና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚመጣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡ ይህ ሐሳዊ መሲህ ብዙዎችን በማሳት በሀሰት መንገድ እየመራ የአመጻ ስራን ያሰራቸዋል፡፡ እነዚህን የአመጻ ስራዎች ለአራት ከፍለን ማየት እንችላለን፡-

1. የሃይማኖትን ድንበር ማፍረስ---አባቶች ያኖሩትን የቀድሞውን ድንበር አታፍርስ፡፡ ምሳ 22÷ 28
2. የስነ-ተፈጥሮ ህግ ድንበርን መጣስ---ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱም አስጸያፊ ነገር አድርገዋል፡፡ ዘሌ 20÷ 13
3. በጋብቻ ላይ የሚደረግ ርኩሰትን---ከዝሙት እንደትርቁ፤ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አህዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ፤ 1ኛ ተሰ 4÷ 4-5
4. ጾምን፣ ጸሎትን፣ መንፈሳዊያንንና መንፈሳዊነትን፣ ሰብዓዊ ክብርን ወዘተ.....ማቃለል---ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ። 2ኛ ጢሞ 3÷ 5

እነዚህንና የመሰሰሉትን አስጸያፊ ተግባራት ያደርጉ ዘንድ ሰዎችን በማሳት ከመንፈሳዊው እስከ ዓለማዊው፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከትልቅ እስከ ትንሽ፣ ሁሉንም ከቅድስና ህይወት ያርቃቸዋል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረውም በዚያን ዘመን ሰዎች መልካምን ነገር የማይወዱ ይሆናሉ፡፡ /2ኛ ጢሞ 3÷ 1-3/ ለዘመናት በአንድነት የኖረችውንም ቤተ-ክርስቲያን ለመከፋፈል ይነሳሉ፣ ፍጻሜያቸው ግን ሽንፈት ነው፡፡ በሐዋርያት መሰረት ላይ የተሰራችውን ቤተ-ክርስቲያናችንን የሲያል ደጆች አይችሏትምና፡፡ /ማቴ 16÷ 18/

ከዚህ ሁሉ ፈታኝ የመከራ ጊዜ በኋላ ግን ጌታ ይመጣል፡፡ መምጣቱም ምልክቶቹን አስተውለው ለተመለሱት፣ ከክፉዎች ጋር ላልተባበሩትና ስለስሙ መከራ ለተቀበሉት ዕረፍት ሚገኝበት፤ ለሐሳዊው መሲህና ተከታዮቹ ግን ወደ ዘላለም ፍርድ የሚገቡበት ነው፡፡ በመሆኑም እኛ ክርስቲያኖች የጥፋት ትንቢቱ መፈጸሚያ እንዳንሆን ራሳችንን ከሀጢአትና ርኩሰት እየጠበቀን፤ በጌታ መምጣት ደስ ከሚላቸው ቅዱሳን ጋር ለመሆን በንስሃ ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ፤ በቤቱም ልንኖር ያስፈልጋል፡፡

"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" ራዕይ 22÷ 12